# “ያልተመረመረ ሕይወት ትርጉም የለውም”፦ የስነ ምግባር መቅድም ለፍትህ ስርአት ባለሙያዎች

ጴጥሮስ ቶጃ*

ስነ ምግባር (Ethics) በኢትዮጵያ የሕግና ፍትህ፣ በሌሎችም ስነ ማኅበራዊና ልቡናዊ የእውቀት ምህዳር ውስጥ በስፋትና በጥልቀት ተገቢ ትኩረት የተሰጠው ክስተት አይደለም። የፍልስፍና አንድ ዘርፍ ቢሆንም ቅሉ፣ ጠቃሚና ሁለ ገብ የጥናትና የእውቀት ርዕስ እንደመሆኑ ለከፍተኛ ደረጃ ተማሪዎችና ለባለሙያዎች ትምህርትና ሥልጠና ውስጥ መመደብ የሚገባው ነው። የሰዎች የባህሪ እድገትና የልምድ በሳልነት በስነ ምግባር እውቀት ጭምር መታነፅ ይገባዋል። ስለዚህም፣ ስነ ምግባር በኢትዮጵያ ማኅበራዊና ባህላዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች አኳያ ትኩረታዊ ጥናትና ምርምር ያስፈልገዋል።

ስነምግባር ምንድንነው? ከግብረ ገብነትስ (morality) እንዴት ይዛመዳል? ወይም ይለያል? ምግባረ ሰናይስ (virtue) ምን ማለት ነው? እነዚህ ጥያቄዎች የሚያነሱአቸው መሰረታዊ ፅንሰ ሃሳቦች ግልፅ መልስ የሚያስፈልጋቸው ናቸው።

ስነምግባር፣ የግል ወይም ማህበራዊ ወይም ሙያዊ ነክ ችግሮችን ለማስተዋል፣ ለመለየት፣ ለመመርመር፣ መፍትሄ ለመስጠት የምንችልበት ዕውቀት ነው።[1] ስነ ምግባር እውነትን ከውሸት አንጥሮ ለመለየት፣ ጎጂውን ከጠቃሚው ደንቃራውን ከቀናው ነገር በንቃት ለመመልከት የሚያስችለንና፤ ተገቢና ሚዛናዊ የውሳኔ አሰጣጥ መመሪያችንና ጥናታዊ እውቀት ነው። ስነ ምግባር ለባህሪያችን እድገትና እንፃት ማለትም በግልና በሙያዊ ሕይወታችን ውስጥ በጎ ምግባርንና በጎ ተግባርን የምንከተልበት፤ እንደ ሰብእ የምንነታችንና የማንነታችን መሠረት መገንዘቢያ የጥናት ማህደር ነው። ኢትዮጵያውያኑ ፈላስፋዎች ዘርአ ያቆብና ወልደ ሕይወት በሐተታቸው እንደሚያትቱም ብርሃነ ልቡናና የሰላ ህሊና እንዲኖረንና የእውቀት ጥበብ እንድንጎናፀፍም ያስችለናል።[2] ስነ ምግባር ከዚህ ቀደም የያዝናቸውን ግላዊ ሃሳቦችና ማህበራዊ እሴቶች(social values) እንደተጨባጭና ተለዋዋጭ ሁኔታዎች እንድንመረምር፣ እንድንገነዘብና እንድናርምም ያግዘናል። ምክንያቱም፣ ስለራሳችንም፣ ስለሙያችንም ሆነ ስለህብረተሰባችን ያለን እውቀት የተሟላ አይደለም። በአጭሩ ፍፁማዊ አይደለንም።

---

*ፕሮፌሰር፣ በአሜሪካን ኩትዝታውን ዩኒቨርስቲ ኦፍ ፔንሲልቬንያ፤ ፀሃፊው የመጽሔቱን የአርትኦት ቦድን አባላት እንዲሁም ለሁለቱ የፅሁፉ ገምጋሚዎች ከፍተኛ ምስጋና ለማቅረብ ይወዳሉ፡፡

[1] See generally Banks, C., *Criminal Justice Ethics: Theory and Practice*, Thousand Oaks, SAGE Publications, 3rd ed., 2013 [Hereinafter ባንክስ]; Williams, R. & Arrigo B., *Ethics, Crime and Criminal Justice,* Prentice Hall, New York, 2007[Hereinafter ዊልያምስና አሪጎ]; Souryal S., *Ethics in Criminal Justice: in Search of the Truth,* Anderson, Cincinnati, 1998; Albanese, J., *Professional Ethics in Criminal Justice: Being Ethical When No One is Looking*, Pearson, New York, 3rd ed., 2012[Hereinafter አልባኒስ].

[2] Sumner, C., *Ethiopian Philosphy: the Teatise of Zara Yakob and Wolde Selassie,* AAU Press, Addis Ababa, 1978, Vol.3, ገፅ 162-3.

ስለዚህም፣ ስነ ምግባር (Ethics) እንደ አንድ የፍልስፍና ጥናታዊ ምርምር ዘይቤ፣ እንዲሁም እንደእውቀት ማህደር ስለግብረ ገብነት (morality) ግብረ ገባዊ እሴቶች (moral values) ላይ ትኩረት የሚሰጥ ነው። ግብረ ገብነት (morality) የሰዎችን ባህሪይ፣ ድርጊትና ዝንባሌ የሚያካትት ነው። ለምሳሌ፣ ቅንነት፣ ደግነት፣ ታታሪነት፣ ተቆርቋሪነት፣ አክባሪነት፣ ርህሩህነት፣ ትሁትነት፣ ግልፅነት፤ ፍትሃዊነት፣ ታማኝነት፣ ቁርጠኛነት ወዘተ። እነዚህ የባህሪይ ገፅታዎች ደግሞ፣ ባብላጫው ግላዊ ሳይሆኑ፤ ማህበራዊ ይዘት አላቸው። የአንድ ሰው ቅንነት፣ ደግነት፣ ታታሪነት፣ ሃቀኝነት፣ ተቆርቋሪነት፣ ወይም ርህሩህነት፣ ወይም ትሁትነት፣ ግልፅነት፤ ወይም ፍትሃዊነት፣ ወይም ታማኝነት፣ ለራሱ ለግሉ የሚያሳየው ወይም የሚገልፀው አይደለም። ለግል ለራሴ ርህሩህ ነኝ ማለት ወይም ደግ ነኝ ማለት ትርጉም የሌለውና ፋይዳ ቢስ ብቻም ሳይሆን ጅልነት ነው፤ አስቂኝም ነው። እነዚህ ባህሪዎች ባብዛኛው የሚገለፁት፣ ሰዎች አብሮ በመኖርና በመስራት በማህበራዊ ህይወታቸው ውስጥ እርስ በርሳቸው ባላቸው የስራ ግንኙነት፣ ጉርብትናና ማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ነው።

## *የስነ ምግባር ጥናት ጠቀሜታው*

በተለይ ለፍትህ ስርአት ባለሙያዎች፣ የስነ ምግባር ጥናት (Ethics) ጠቀሜታው ምንድን ነው? በዚህስ ጥናትና እውቀት ዳኞች፣ ጠበቆች፣ አቃቤያነ ህግ፣ ፖሊሶች፣ የህግ አማካሪዎችና አስተዳዳሪዎች ምን ይጠቀማሉ? ከህብረተሰቡና ምንስ ይጠበቅባቸዋል? የተረከቡት ሃላፊነትስ ምንስ ያስገድዳቸዋል?

ስነ ምግባር ማጥናት፣ የግብረ ገብነትን ወይም የስነ ምግባርን ብልሹነት በራሱ አያሳይም ወይ? የሚል የቅሬታ ጥያቄ አለ። ስነ ምግባርን ማጥናት በቀጥታም ይሁን በአንደምታ የባህሪይ ብልሹነትን አያሳይም። ለምሳሌ፣ አንዳንድ የአሜሪካ ፖሊሶች ስነ ምግባርን በተመደበላቸው ሥልጠና ውስጥ አጥኑ ሲባሉ፣ ብልሹ ስነ ምግባር ተጠናውቶአችኋል የማለት ያህል አይደለም ወይ? ብለው ይቆጣሉ። ሆኖም፣ ይህ ጤናማ (ትክክለኛ) አስተሳሰብ አይደለም፡፡ ይልቁንም አስተሳሰቡ ከስጋት የመነጨ ነው፡፡ እነሱ እንደሚያስቡት ስነ ምግባር ማጥናት የስነ ምግባር ብልሹነት ማስረጃ ሳይሆን፣ ባለሙያዎች በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ ላይ መልካም ስነ ምግባር ኖሮአቸው፣ ፍትሃዊና ስኬታማ ተግባሮችን በማከናወን ህብረተሰቡን በትጋት ለማገልገል የሚያስችላቸው ነው። ለዚህም የማነፃፀሪያ ምሳሌ ለመስጠት፣ አንድ ሀኪም ህክምና የሚያጠናው ህመምተኛ ስለሆነ ወይም በሽታ ስለተጠናወተው አይደለም። ይልቁኑስ የህክምና እውቀትና ችሎታ ይዞ የጤና ምክር ለመስጠት፣ በሽተኞችን ለማከምና ከበሽታ ለመከላከል ነው።

በተመሳሳይ፣ የፍትህ ሥርአቱ ባለሙያዎችም፣ ዳኞች፣ ዓቃብያነ ህግ፣ ጠበቆች፣ ፖሊሶች፣ የማረሚያ ቤት አስተዳዳሪዎችና ሠራተኞች (ስታፍ) ከሙያ እውቀታቸውና ሥልጠናቸውና ጋር ስነ ምግባር ማጥናት የሚገባቸው፣ ለሕዝብ የተሻለ ማህበራዊ አገልግሎት ለመስጠትና የሙያ ኃላፊነታቸውን በአግባቡና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለመወጣት እንዲችሉ ነው። ምን ጊዜም እውነትን እንዲሹ፤ አርቆ አሳቢ እንዲሆኑ፤ ሥኑይና እኩይ ጠባይና ተግባሮችን እንዲለዩ፤ ሥራቸው ስኬታማና ፍሬያማ እንዲሆን፤ ለሌሎች ተምሳሌ እንዲሆኑ፤ ለሕዝብ ተቆርቋሪና ተሟጋች እንዲሆኑ፤ በጥሩ ሥራቸውና በኃላፊነታቸው ተመስጋኝ እንዲሆኑ፣ ሲያጠፉ ደግሞ ተጠያቂ (accountability) ለመሆን እንዲችሉ፤ ለግልፅነት (transparency) ፈቃደኝነት እንዲያሳዩ፤ ተደራሽነትንና (accessibility)፣ በአገልግሎታቸው ከሕዝብ ተዓሚነትን (legitimacy) እንዲጎናፀፉ ነው።

## *"ያልተመረመረ ሕይወት ትርጉም የለውም"*

ሶቅራጥስ፣ ጥፋተኛ ነህ ብለው ለፈረዱበት የሕዝብ ዳኞች (jury) ቅጣቱን እየተጠባበቀ ሳለ በሰጠው መልስ፣ "ያልተመረመረ ሕይወት ትርጉም የለውም" ይላል።[3] የጥቁር አሜሪካውያን መብት ተሟጋች ሆኖ በተቃዋሚዎቹ የተገደለው፤ ማልከም ኤክስ ደግሞ በ1960ዎች አያይዞ፣ "የተመረመረ ሕይወት መራር ጎምዛዛ ሊሆን ይችላል" ይላል። ጥንታዊው የግሪክ ፈላስፋ ሶቅራጥስና ጥቁር አሜሪካዊው ማልከም ኤክስ በ2300 አመታት ይራራቁ እንጂ የስነ ምግባር አስተያያታቸው ተደጋጋፊ ነው፤ ለፍትህና ለእውነት ያላቸው ፅናት ተምሳሌ ጠቢባን አድርጓቸዋል። ማልከም በትምህርቱም ሁለተኛ ደረጃን ያላጠናቀቀና አሜሪካን ውስጥ በሃያ አመቱ በተራ ወንጀሎች የአስር አመት እስራት ተፈርዶበት፣ ማንነቱን አገላብጦ መርምሮ ሕይወቱን ሙሉ በሙሉ ያስተካከለው፣ ትምህርታዊ ጥናት ያካሄደውና የጥቁሮች መብት ትግል ታዋቂ መሪ ለመሆን የበቃው ከእስር ቤት ውስጥ ነው።

ማልከም ኤክስ፣ በሕይወቱ ውጣ ውረድ ውስጥ ማንነቱን ባጠቃላይ ሲገመግም እንዲህ ይላል፥ "እኔነቴን እኔ ያሰኘኝ ምንድነው? ማንኛውንም ሰው በሚገባ ለማወቅ፣ ማንነቱን ከትውልዱ ዕለት ጀምሮ መመርመር ያስፈልጋል። በሕይወታችን ያጋጠሙን ልምዶች ሁሉ ባህሪአችን ውስጥ ዘልቀው ተዋህደዋል፤ ማንኛውም የኑሮ ገጠመኝ በማንነታችን ውስጥ ተቀርፆአል"።[4]

ሶቅራጥስ በሰባ አመት እድሜው በአቴናውያን ሁለት የወንጀል ክስ ተመስርቶበት የሞት ብያኔ ተፈረደበት። አንደኛው ክስ ለግሪክ አማልክት አክብሮት የለውም የሚልና ሁለተኛው ደግሞ ሶቅራጥስ የሚያስተምረው ትምህርት በመናፍቅነት የወጣቱን አእምሮ እየበከለ ነው የሚል ክስ ነው።[5] እነዚህ ክሶች የቀረቡበትና የሞት ቅጣቱ ደግሞ የተፈፀመው የዲሞክራሲ ሥርዓት በተፀነሰባት ታሪካዊ አቴንስ ከተማ ውስጥ ነው። ሶቅራጥስ የሞት ፍርዱን እየተጠባበቀ በእስር ላይ ሳለ፣ ወዳጆቹና ተማሪዎቹ ከእስር ሊያስመልጡት ቢሞክሩም አሻፈረኝ አላቸው። እምቢ ያለበትም ምክንያት፣ ከሕግ ፊት ማምለጥና ከፍርድ ብያኔ በመሸሽ መልካም ምሳሌ መሆን አይቻልም ሲል ነው። ከጠቢብነቱ በላይ ሶቅራጥስ በፅናቱና በድፍረቱ የምግባረ ሰናይ አርአያ ለመሆን ሕይወቱን አሳለፈ፤ የሞት ቅጣቱን በፀጋ ተቀብሎ መርዙን (ሄምሎክ) ጠጣ። አንድ ማለዳ ላይ ወዳጁ ክሪቶ እስር ቤት መጥቶ፣ ሕይወቱን ለማትረፍ ከሞት እንዲያመልጥ ሲያወያየው፤ የሶቅራጥስ መልስ፣ "ይበልጥ የሚያስቸግረው ከሞት መሸሽ ሳይሆን፣ ይልቁንስ አዳጋቹ ነገር ከእኩይ ተግባር መራቅ ነው"።[6]

---

[3] Plato, *The Last Days of Socrates,* Penguin, Middlesex, 1959, ገፅ 72 [Hereinafter ፕላቶ].

[4] Malcolm X. & Haley, *The Autobiograhpy of Malcolm X*, Grove Press, New York, 1966፣ ገፅ 153 [Hereinafter ማልከም ኤክስና አሌክስ ሄሊ].

[5] ፕላቶ ፣ Maclntyre, A., *A Short History of Ethics*, Macmillan, New York, 1966 (Hereinafter ማክንታየር)፣ Lavine, T, *From Socrates to Sartre: the Philosophic Quest*, Bantam, New York, 1984 (Hereinafter ሌቪን) ይመለከቷል፡፡

[6] ፕላቶ፣ ገፅ 73

ለሶቅራጥስ፣ መልካም ኑሮ (good life) ለመኖር የራስን ስነ ምግባር እውቅና (self-consciousness) ለዚህም "ምን አይነት ባህሪይ አለኝ?" ለሚለው ጥያቄ በራስ ላይ ሂሳዊ ግንዛቤን (critical reflection) ሳያቋርጡ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ለሶቅራጥስ እውቀትና ጥበብ ተያያዥ ናቸው፤ እውቀትና ጥበብም የእውነት መፈለጊያ ቁልፍ ናቸው። እውቀትን መጎናፀፍ ማለት እውነትን መጎናፀፍ ነው። ምግባረ ሰናይነት የእውቀት ጥበብ ነው። የሚደንቀው ነገር፣ ከአቴናውያን ጠቢቦች ሁሉ ታላቅ ጠቢብ ለሚባለው ፈላስፋው ሶቅራጥስ፥ ለእርሱ ዐቢይ የግል እውቀትና "የእውቀት መነሻ መሠረቱ በበቂ አለማወቁን ማወቁ ነው"።[7]

ይህ የሚያስገነዝበን፣ አለማወቅን ማወቅ የአዋቂነት መመዘኛ ሆኖ መታየቱ ሶቅራጥሳዊ የስነ ምግባር ጥበብ እንደሆነ ነው። የሰው ልጆች በእውቀታቸው ፍፁማዊ አይደሉም። እንደ ፈሪሳውያን አዋቂዎች ነን ወይም ብፁአን ነን ብሎ መመፃደቅም ትዝብት ላይ ይጥላል። ሶቅራጥስ እንደሚያስገነዝበው፣ "ሰዎች የሚሳሳቱት ሆን ብለውና አውቀው ሳይሆን ካለማወቅ ከሚደርስ የስነምግባር ደካማነት ነው" ይላል።[8] ስለዚህም በእንደዚህ አይነት አላዋቂነት ምክንያትም ሰዎች በሚሉትና በሚሰሩት መካከል በሚከሰት ሰፊ ገደል ስር ግብረ ገባዊ መንሸራተት (moral lapse) ይታይባቸዋል።[9]

ስለዚህም ነው ሶቅራጥስ "ያልተመረመረ ሕይወት ትርጉም የለውም" ያለው። አንደኛ፣ የሰው ልጅ የግልና ሙያዊ ጠባይ እንደማህበራዊ ገጠመኙ ምንጊዜም ተለዋዋጭ በመሆኑ፤ ሁለተኛ፣ የሰው ልጅ በኑሮው በርካታ ፈተናዎችና ችግሮች ስለሚያጋጥሙት እነዚህን ለመፍታትና ውጤታቸውንም ለመገምገም አስፈላጊ በመሆኑ፤ ሦስተኛም ራስን ጠንቅቄ አውቃለሁ ብሎ ማለት እንደማይቻል፤ ይህ ቢሆንማና መልካችንና ቁመናችንን ያለጥርጣሬ ብናውቀው ኖሮ፣ ለምሳሌ ምን መስለን አደባባይ እንደምንወጣ መልካችንን በመስታወት ነጋ ጠባ ማየት ባይገባንም ነበር። ከመስታወት ትዩዩ ፊታችን ላይ የሚታይ ጉድፍ ለማንሳት፣ ፀጉራችንን ለማሰማመርና አለባበሳችንን ለማስተካከል በየእለቱ ባልተጨነቅንም ነበር።

በተነፃፃሪ ራሳችንን የምንመረምርበት የባህሪና የስነ ምግባር መስታወት ያስፈልገናል። ይህም ማህበራዊ መስታወት፣ የስነ ምግባር (Ethics) ጥናትና እውቀት ነው። ከባልንጀራ፣ ከቤተሰብ፣ ከሙያ ባልደረቦቻችንና ከዜጎች የሚቀርቡልንን ምክሮች፤ ማረሚያ ሃሳቦችና ትችቶች ሁሉ አዳምጠን በትጋት ማጤን ይኖርብናል። በመስታወት መልካችን ሸጋ ባይመስል ቅር የሚለንን ያህል ደግሞ፣ ምግባራችንን ስንመረምር ያልጠበቅነው ሆኖ ካገኘነው ደግሞ ሊከፋን ይችል ይሆናል። ለዚህም ነው በማልከም ኤክስ ግንዛቤ፣ "የተመረመረ ሕይወት መራራ ሊሆን የሚችለው" ያለው።

ምክንያቱም፣ ከሠሩ መሳሳት አለ፤ ፍፁማዊ አይደለንም። የግል ጥቅማችን ወይም የግል ፍላጎታችን ከሌሎች ሰዎች ፍላጎት ጋር ሊጋጭ ይችላል፤ ከማህበራዊ ግዴታችን ጋር ሊቃረን ይችላል። እንደሰብእ የግል ህይወታችን በማህበራዊ ሕይወት የተከደነ ነው።ስለዚህም በግል ሕይወታችንና በማህበራዊ ግዴታችን መካከል ሊኖር የሚገባውን ሚዛን መጠበቅ ይገባናል። ከግል ጥቅማችን ባሻገር ሁላችንም በግልና በጥቅል ለተረጋጋ ሰላማዊ ማህበራዊ ሥርዓት መጣጣር ይኖርብናል፣ የግል ጥቅምና ፍላጎት መኖሩና መከበሩ ደግሞ አጠያያቂ አይደለም። ፍጹም ግለኝነት

---

[7] ማክንታየር፣ ገፅ 19

[8] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 23ን ይመልከቱ

[9] ዝኒ ከማሁ

ደግሞ አፅናፋዊ ሆኖ የግል ጥቅም መስመር ከያዘ ከማህበራዊ ሕይወት ጎዳና ውጭ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም፣ ከታች ዝቅ ብለን እንደምናየው፤ የጋራ ማህበራዊ ሥርዓታችን አለመረጋጋት የመጨረሻ የመጨረሻ የየግል ጥቅማችንን ጭምር ይንደዋል። የእኔነቴ ህልውና ማህበራዊ ነው፤ የማህበራዊነቴ ህልውና ደግሞ እኔነቴን ይገልጸዋል። የዚህ አያያዥ ውል ደግሞ ባብላጫው ማህበራዊ መሠረት ያለው ስነ ምግባር ነው።

በዚች፤ የስነ ምግባር አጭር ጥናታዊ መጣጥፍ ሆነ የአንድ ቀን ሴሚናር ደግሞ ስነ ምግባርን አንጎናፀፍም፤ ይልቁንም በዚች ምድር በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ሳናሰልስ የምናዳብረው፣ የምንመረምረውና የምናስተካክለው ነው። የእያንዳንዳችን ያልተቋረጠ ምርምርና ግንዛቤ እንዲሁም ለመታረም ካለ ቅን ፍላጎት ላይ ተመስርተን ስነ ምግባራችንን ማጎለበት ይኖርብናል። ይህ ደግሞ ደካማነትን አያሳይም፤ እንዲያውም ብርቱነትን፣ ደፋርነትንና የባህሪን ጠንካራነት ነው የሚያሳየው። በተቃራኒው፣ ፍፁማዊ በሆነ ስሜት እርማት አያስፈልገኝም፤ ጉድለት አይኖረኝም ብሎ ማለት ግን ደካማነት ነው።

## *ስነ ምግባር (Ethics) ምንድነው?*

*ኤቲክስ፣ ኤቶስ ወይም ኤቲኮስ ወይም ኤቲካ* ከሚለው የግሪክ ቃል የመነጨ ሲሆን፣ ባህሪ ወይም ጠባይ ማለት ነው። ይህም ትኩረቱ በተለይ ስለሰዎች ባህሪ የሆነ የፍልስፍና ጥናት አንድ ዘርፍ ሲሆን፣ ሦስት ክፍሎች አሉት[10]:- 1) *የቢሆን ስነ ምግባር* (Normative ethics) ምግባራችንና ተግባራችን ምን መሆን ይገባዋል? ምን ማድረግ ይገባኛል? ምን አይነት ባህሪ ሊኖረኝ ይገባል? እና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ በመሻት በጎ ምግባርን እንድናንፅ፤ መልካም ተግባሮችን እንድናከናውን ያሳውቀናል። 2) *ልዕለ ስነ ምግባር* (Metaethics) – ሁለገብና ከፍተኛ ስነ ምግባራዊ ጥያቄዎችን እንድናነሳና ትንታኔ እንድናደርግ ይጠቅመናል። ስነ ምግባር ከየት መነጨ? ለውሳኔዎቻችን በርግጥ የግል ምርጫዎች አሉን? ስነ ምግባራዊ ይዘት በማህበራዊና በባህላዊ አስተሳሰብ ላይ ተመስርተው የታነፁ ናቸውን? ስነ ምግባራችን ከግል ጥቅም ጋር የተያያዙ ናቸውን? በግል ጥቅም ላይ ተመስርተዋልን? እና የመሳሰሉትን ሁለንተናዊ ጥያቄዎች አንስተን በልቡናችን እንድንመረምር ይረዳናል። 3ኛም፣ *ገቢራዊ ስነ ምግባር* (Applied ethics) - በተቀዳሚ ግብረ ገባዊ ጉዳዮች (ethical issues) እና በግብረ ገባዊ አጣብቂኞች (ethical dilemmas) ላይ፣ በግልና በሙያዊ ሕይወት የሚቃለሉና መፍትሄ የሚያስፈልጋቸው ችግሮች ላይ እንድናተኩርና መልስም እንድንፈልግላቸው አቅጣጫ ያሲዙናል።

በቀዳሚ ደረጃ የሚመደቡ ስነ ምግባራዊ ጉዳዮች (ethical issues) ከፍ ባለ ይዘታቸው ህብረተሰብን ወይም የማህበራዊ ክፍሎችን የሚመለከቱና በፖሊሲ ደረጃ መልስ የሚሰጥባቸው ናቸው።[11] ከነዚህም መካከል ለምሳሌ፣ የሞት ቅጣት ተገቢነት፣ የእስራት ቅጣት እንደጠባይ ማረሚያ ፍሬያማነት፣ በአመክሮ መልቀቅን በእስር ቤት አማራጭነት (parole and probation)፣ የወንጀለኛ

[10] ባንክስ 2013፣ ዊልያምስና አሪጎ 2007፣ በአጠቃላይ ክፍል ሁለትና ሶስት

[11] ባንክስ፣ ገፅ 11-2.

ቅጣቶች እንደወንጀሉ ክብደት ተመጣጣኝነት (priniciple of proportionality)፣ የገንዘብና የሕግ እውቀት ችግር ላላቸው ዜጎች የፍትህ ተደራሽነት (access to justice)፣ ወዘተ።

ስነ ምግባራዊ አጣብቂኞች (ethical dilemmas) ደግሞ በሙያ ኃላፊነት ምድብ፣ እንደ ዳኛ፣ አስተዳዳሪ፣ ጠበቃ፣ የፖሊስ መኮንን በግል የሚያጋጥሙና የሚደርሱ ውሳኔዎች ወይም ችግር አፈታቶችን የሚጠቀልሉ ናቸው።[12] በወንጀል ፍትህ ባለሙያዎች የእለት ተእለት ውሳኔዎችና እርምጃዎች የሚያጋጥሙ ናቸው። ለምሳሌ፤ ተጠርጣሪን አስሮ ፖሊስ ጣቢያ መውሰድ ወይም እንዳይለመድህ ብሎ በማስጠንቀቂያ መልቀቅ፤ መፈተሽ ወይም አለመፈተሽ፤ ኃይል መጠቀም ወይም አለመጠቀም፤ ዓቃቤ ሕግ ክስ መመስረትና ማስቀጣት፤ ዳኞች የጥፋተኝነት ፍርድ መበየን አለመበየን፤ የማረሚያ ቤት አስተዳዳሪዎች በተግሳፅ የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰድ ወይም የታራሚውን ቀና ባህሪ ማበረታታት የመሳሰሉትን ውሳኔዎችንና እርምጃዎችን ይመለከታል። ከእነዚህ ስነ ምግባራዊ አጣብቂኞች ከስነ ምግባራዊ ንድፈ ሃሳቦች አኳያ ለመወጣት ባጠቃላይ የሚረዱ የመፍትሄ ስልቶችን ዝቅ ብለን እናያለን።

ግብረገባዊ ባህሪዎች ሁለንተናዊ (ethical universalism) እና አንፃራዊ (ethical relativism) ተብለው ይፈረጃሉ።[13] በአንድ በኩል የሰዎች ግብረገባዊ ባህሪዎች ሁለንተናዊ (universal) ሆነው ይታያሉ። ለምሳሌ፣ ለሰው ልጅ ሕይወት ክብር መስጠት፣ ለሕፃናት እንክብካቤ ማድረግ ወዘተ። በሌላ በኩል ግን፣ የሰዎች ግብረገባዊ ባህሪዎች ታሪካዊና ባህላዊ ቅኝት አላቸው የሚል አስተያየት አለ። በዚህም ምክንያት ሁለንተናዊ ከመሆን ይልቅ በቦታና በጊዜ አንፃራዊ ገፅታ ይኖራቸዋል። ለምሳሌ፣ በታሪክ 'ድፍረት' (courage) ለሚለው ምግባር (በግሪከኛ 'አጋቶስ')ከጥንታዊ ግሪክ ህብረተሰብ ጀምሮ ከዘመን ዘመን ትርጉሙ፣ ጀግንነት፣ ጦረኛ፣ ችሎታ፣ ቀና ባህሪ፣ ወዘተ በሚል ስነ ምግባራዊ መመዘኛነት ሲለዋወጥ ተመዝግቧል።[14] ከዚህም ሌላ፣ በታሪክ እንደማህበራዊ ሥርዓት ለውጥ የትርጉም ተለዋዋጭነት ብቻ ሳይሆን፤ እንደየባህሉ ልዩነት በአንድም ወቅት ደግሞ ስነ ምግባሮች አንፃራዊ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ታዳጊ ህፃናትን በለጋ እድሜያቸው በሥራ መስክ ማሰማራት፣ ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ሴቶችን ለትዳር መዳረግ፣ ነፍሰ ገዳይ ወንጀለኞችን በሞት ፍርድ መቅጣት ወዘተ። በዚህም ምክንያት አንፃራዊ ተግባሮች ከሁለንተናዊ ስነ ምግባር ይዘቶች ጋር የሚመሳሰሉትን ያህል በግልፅ ይጋጫሉ።

ለፍትህ ሥርዓት ባለሙያዎች፣ ገቢራዊ ስነ ምግባር እነዚህን የመሳሰሉ ተግባራዊ ችግሮችን ለማቃለል የሚያስችሉ እውቀትና ልምድ እንድናካብት ይረዱናል። ይሁንና መልሶቻችን አከራካሪም ስለሚሆኑ ከስሜታዊ ውሳኔ መቆጠብ ደግሞ የግድ ነው። ለዚህ ተግባራዊ ስነ ምግባር ደግሞ፣ የቢሆን(ኖርማቲቭ) ስነ ምግባርና ላዕላይ ስነ ምግባር መንገድ ቀያሾች ናቸው። ከዚህም ላይ በመነሳት፣ የስነ ምግባር እውቀትና ምርምር አስፈላጊ ነው። አለበለዚያ፡- በአንድ በኩል፣ አንድ የህክምና ተማሪ የሰው አካላት ልዩ ልዩ ክፍሎችንና አሠራራቸውን ሳያውቅ በሽታ ለማዳን ተሽቀዳድሞ ቀዶ ጥገና ለማድረግ እንደሚሞክር ያህል ነው። በሌላ በኩል፣ የስነ ምግባር እውቀትና ስልጠና ሁልጊዜም የሚተኮርበት እንጂ፣ ስህተት ከተሠራ በኋላ እንደ መፈወሻ መድኃኒት እንክብል የሚዋጥ አይደለም። ጤናማ ሆኖ ለመኖር፣ ሲታመሙ ብቻ መድኃኒት በመውሰድ ብቻ አይደለም

[12] ዝኒ ከማሁ

[13] ዝኒ ከማሁ፣ገፅ 6-8.

[14] ማክእንታየር፣ገፅ 5-9.

መፍትሄ የሚገኘው። የአመጋገብን፣ እረፍትንና የስፖርት እንቅስቃሴን ዘይቤ በመከተል አስቀድሞ ከአንዳንድ አይነት ህመም ለመከላከል እንደሚቻለው ሁሉ፣ የስነ ምግባራዊም ንቁ ኅሊና ከአንዳንድ የስራ ነክ ስህተቶች አስቀድሞ ለመጠንቀቅና ለመከላከል ያስችላል።

የስነ ልቡና ተመራማሪ የሆነው ሎረንስ ኮኽልበርግ[15]፣ የጂ ፒያዤን ስነ ልቡናዊ የእድገት ደረጃዎች ላይ ተመስርቶና አስፋፍቶ (ወንድ ወጣቶች ላይ ባደረገው ጥናት) የግብረገባዊ (ሞራላዊ) እድገት ደረጃዎችን በስድስት ከፍሎ እንደሚከተለው ያስቀምጣቸዋል፡-

አንደኛ፣ የደመ ነፍስ ስነ ምግባር የሚለው በለጋ ልጅነት እድሜ ስነ ምግባር በቅጣት ወይም በግሳፄ ፍርሃት የሚቀረፅ ነው። ይሁንና፣ ልጁ የቀጭውን ኃይልና ቁጣ እንጂ መስተካከል የሚገባውን ጠባይ ምን እንደሆነ አይረዳውም። በዚህ ደረጃ፣ በፍርሃትና በጭፍን ትእዛዝ ይቀበላል። ለእዚህ ምሳሌ፣ አንድ የቅርብ ወዳጄ ልጅ የሁለት ዓመት ህፃን ሳለ፣ በጣቱ ግድግዳ ላይ ያለ የኤሌክትሪክ ሶኬት (power outlet) ሲኅረጉር፤ አባቱ ተው ብሎ እጁን ይመተዋል። ሕፃኑም እጁን ወደኋላ አሸሽቶ፣ እንደገና ሶኬቱን በምላሱ ለመነካካት ይሞክራል። ይህ ሕፃን በደመ ነፍስ ግንዛቤው የጥፋቱ መንስኤ ከኮረንቲ መንካት አለመቆጠብ መሆኑን አለመረዳቱ ላይ ነው።

ሁለተኛው፣ ግለኝነትና የግል ጥቅም የሚዳብርበት የሞራል ደረጃ ሲሆን ግለሰቦች ድርጊቱ ለራሳቸውና ለሌሎች ሊያስከትል የሚችለውን ጥቅምና ጉዳት (ደስታ ወይም ስቃይ) (hedonistic calculus) ማመዛዘን ይጀምራሉ። ሦስተኛም፣ ግለሰቦች ማህበራዊ ማበረታቻ (ከቤተሰብ፣ መምህራን ወዘተ.) ሲያገኙ የሚጠበቅባቸውን ምግባር ያሳያሉ፤ የሚያስመሰግናቸውን ተግባር ይፈፅማሉ፤ የሚያስነቅፋቸውን ይተዋሉ። አራተኛው ደረጃ የህግና ሥርዓት ግንዛቤ ደረጃ ሲሆን፣ የህግንና ህጋዊ ባለሥልጣንን መፍራትና ማክበርንና (ለምሳሌ፣ የንብረት ስርቆት የሚያስቀጣ ህግን የመጣስ ድርጊት ስለመሆኑ) መገንዘብን ያሳያል። አምስተኛው፣ በማህበራዊ ውል (social contract) የላቀ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ እንደዜጋ መብትና ማህበራዊ ግዴታን ማወቅ ይጠቀልላል። ስነ ምግባራዊ አስተሳሰብን ረቀቅ ባለ መልኩ መገንዘብ ይቻላል፤ መብት፣ ፍትህ፣ ርትዕ ወዘተን ይለያሉ፤ ህጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ያውቃሉ፤ እነዚህ የተመሠረቱባቸውን መርሆዎች ምንነትና ጠቀሜታ ይረዳሉ።

በመጨረሻም፣ ስድስተኛው ላቅ ባለ ደረጃና መልኩ የፍትህንና ርትዕን እንዲሁም የመብትን ሰብዓዊነትን ጉዳዮች ይገነዘባሉ፤ ስነ ምግባርን በጥልቀት ይረዳሉ፣ ይተነትናሉ። ለምሳሌ፡- በፍርድ ለወንጀል ጥፋተኝነት በህጋዊ እውነት (judicial truth) እና ሞራላዊ እውነት (moral truth) ያለውን መሠረታዊ ልዩነት ለመተንተን ይበቃሉ። ህጋዊ እውነት በፍርድ ቤት ችሎት ሂደት በሚቀርቡት ማስረጃዎችና የሕግ ምስክሮች እንዲሁም የጠበቆች ሙግት የተከሳሹ ጥፋት፣ ወንጀለኛ መሆን አለመሆኑ የሚረጋገጥበት "እውነት" ነው። ወንጀለኛው ተበይኖበት ጥፋተኝነቱ ቢረጋገጥበትም፣ ከወንጀሉ ነፃ ሊሆን ይችላሰል። ባንፃሩም፣ ጥፋተኛ አይደለም የሚል ፍርድ (ህጋዊ እውነት) ቢበየን፣ ተከሳሹ ራሱ በውስጠ ህሊናው በርግጥ ልቡ ከሚያውቀው ጥፋተኝነቱ (ሞራላዊ እውነት) ጋር የማይመሳሰልና የሚጋጭ ነው። በዚህም ምክንያት በፍርድ ሥርዓት ውስጥ አንዳንድ ጊዜ፣ ሞራላዊ እውነት በሕጋዊ እውነት ሽፋን ይጋረዳል። ይህ ሊሆን መቻሉን መገንዘብና መቀበል ደግሞ የላቀ ስነ ምግባራዊ እውቀትና ሚዛናዊነት ችሎታ ይመሰክራል።

[15] Kohlberg, L. 'The Claim to Moral Adequacy of a Highest Stage of Moral Judgment' *Journal of Philosophy*, Vol. 70, No. 18, 1973, pp. 630–646

የፍትህ ባለሙያዎች ያካበቱት እውቀትና የሥራ ልምድ በአምስተኛውና በስድስተኛው ደረጃ ክልል ውስጥ ያስመድባቸዋል። ስለዚህም ነው ከታች ዝቅ ብለን እንደምናየው፤ ከዚሁ ጋር ተደርቦ ከፍ ባለና በላቀ የስነ ምግባር መመዘኛዎች ሊታዩ ወይም ሊመዘኑ የሚገባቸው። ሆኖም፣ ካሮል ጊሊጋን "ለየት ባለ ድምፅ"[16] በሚለው መፅሐፏ፣ በአንስታይ (feminist) አመለካከት፣ የኮኽልበርግን ንድፈ ሃሳብ በወንድ ወጣቶች ብቻ የጥናት ናሙና (ሳምፐል) ላይ የተመሠረተና ውሱን ተባዕታዊ አመለካከት ያለው ነው ትላለች። በተለይ ኮኽልበርግ፣ የሴቶች አጠቃላይ የሞራል እድገት፤ ሴቶች ካዳበሩት የርኅራሄ ስነ ልቡናዊና ማህበራዊ ልምድ አንፃር፣ ከላይ ከተዘረዘሩት ሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃ እድገት ከፍ አይልም ስላለው፤ በጠነከረ ትችቷ፣ አንስታይ የሞራል አመለካከት ለየት ባለ መልክ፤ በሴቶች ልዩ ማህበራዊ ልምድና እውቀት አኳያ የተንከባካቢነት ስነ ምግባርን (ethic of care) ይገልፃል እንጂ ዝቅተኛ አይደለም ትላለች።

## *የሕግና ስነ ምግባር ዝምድናና ግጭቶች*

ሕግ እስካለ ስነ ምግባር ለምን አስፈላጊ ሆነ? ሕግ ስነ ምግባርን አያጠቃልልም ወይ?

ለእነዚህ ተዛማጅ ጥያቄዎች፤ ኸርበርት ሀርት እጅግ አጠር ባለች "ሕግ፣ ነፃነትና ሞራሊቲ"[17] መፅሐፉ ውስጥ አጠናቅሮ መልስ ሰጥቶባቸዋል። ግብረ ገብነት (ሞራሊቲ) በርግጥም በሕግ ላይ ተፅእኖ አለው። በወንጀል ሕግ ኢግብረ ገባዊ ባህሪዎችን መቅጣትን ሕጋዊ ግብረ ገብነት (legal moralism) ይለዋል።[18] የራሴን ምሳሌ ለመስጠት፤ በተለያዩ ጊዜያትና ህብረተሰቦች የአልኮሆል መጠጥ እገዳ፣ ሕብረ ትዳር (ፖሊጋሚ)፣ ዝሙትነት፣ ፅንስ ማስወረድ፣ መናፍቅነት፣ የሴት ግርዛት፣ አመንዝራነት፤ ጥንቆላንና የመሳሰሉት ተግባሮች በሕግ እንደወንጀል ተደንግገው ያስቀጡ ነበር፤ በአንዳንድ ቦታ አሁንም ያስቀጣሉ። በግልባጩም፣ ሕግ በማስፈራሪያነትና በቅጣት ጭምር ግብረ ገባዊ ጉዳዮችን ይጠቀልላል። በዚህም ምክንያት ሞራሊቲና ሕግ የሰዎችን ባህሪይ፣ መብትና ግዴታዎች ስለሚመለከቱ ተመሳሳይ መዝገበ ቃላትም ሊጋሩ ይችላሉ)።[19] ለዚህም ምሳሌ የሚሆኑት በኢትዮጵያ ቀደም ሲል፣ ወንጀል የሠራ እንደ ኃጢአት የሠራ ሆኖ ይገለጽ እንደነበር፤ በምርመራና ፍርድ ሂደት የቃል አጠቃቀሞችም፤ እንደኑዛዜ፣ የእምነት ክህደት ቃል፣ መሃላ፣ ወዘተና በአሜሪካም እንዲሁ፤ ማረሚያ (የእስር) ቤቶች penitent ከሚለው ትርጉሙ 'ከኃጢአት ያስተሰርያል' በሚለው ቃል ተመሳስለው penitentiary በሚል እስካሁን ይጠራሉ።

ባንድ ገፅታው፣ ግብረ ገብነት (ሞራሊቲ) ሕግ ላይ ተፅእኖ ያለውና በሌላ ገፅታው ሕግም ግብረ ገብነትን ለማስፈፀም መጠቀሚያ መሆኑን አንዳንድ ፈላስፋዎች ይደግፉታል። ለምሳሌ፣ ጃን ስቱዋርት ሚል "ስለነፃነት" (On Liberty) በፃፈው መፅሓፉ ውስጥ፣ የሕግ መቅጫ አግባብነቱ

[16] Gilligan, C., *In a Different Voice: Psychological Theory and Women's Development*, Harvard University Press, Cambridge, 1982, ገፅ 19-20 ይመለከቷል።

[17] Hart, H. L. A., *Law, Liberty, and Morallity*, Stanford University Press, Stanford, 1962 [Hereinafter ሀርት ]

[18] ሀርት፣ ገፅ 6.

[19] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 2

የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል ከጉዳት እስከተከላከለና እስካልጎዳ ድረስ[20] ከሚል ማገኛ ወይም መመዘኛ አንፃር ነው። በሌላ በኩል እንዲሁም፣ የህብረተሰቡን ሰላምና መረጋጋት እስከጠበቀም ጭምር የህግ አስፈፃሚነት ይደገፋል ።[21]

ይህ ሁሉ ሆኖም ደግሞ፣ ሕግን የሚደነግጉት ሰዎች ስለሆኑ፣ አንዳንድ ጊዜም በታሪክ እንደታየው ሕጎች ከስነ ምግባር ጋር ከመደጋገፍ ይልቅ በቀጥታ ይጋጫሉ። በታሪክ እንደዚህ አይነት የሕግና የሞራሊቲ የከረረ ግጭት ለምሳሌ በሕግ ከተደነገጉት ኢ-ግብረ ገባዊ ድንጋጌዎች መካከል በዘረኛው የአፍሪካነር አፓርታይድ ሥርዓት በደቡብ አፍሪካ፣ የአፍሪካውያን ባርነትና በጥቁሮች ላይ የዘር አድልዎ ጂም ክሮው ሥርአት በአሜሪካ፣ የአርያን ነጭ ዘረኝነት በናዚ ጀርመን፣ የአውሮፓውያን ቅኝ ገዢነት፣ በሴቶች እኩልነት ጉዳይ የመምረጥ መብትን የመንፈግና ግልጽ የፆታ አድልዎ ወዘተ ጥቂቶች ናቸው። እነዚህን ግጭቶች ግብረ ገባዊ በሆነ አቅጣጫ ለመፍታት መቃወም ማለት የተደነገጉትን ህጎች መጣስ ተገቢ ሊሆን ነው። ይህ ሲሆን ደግሞ ቅጣትና እስራት ወይም ሞት ሊያስከትል ይችላል። በዚህም ስነ ምግባራዊ አቋማቸው የተደነገጉ ህግጋት ጥሳችኋል ተብለው እነኔልሰን ማንዴላ፣ ማህተመ ጋንዲ፣ ኢትዮጵያዊው አቡነ ጴጥሮስ፣ ፍሬድሪክ ዳግላስ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር፣ ሮዛ ፓርክ፣ ማለከም ኤክስ ወዘተ የተንገላቱት፤ ተንገላተዋል፤ ታስረዋል፤ ሞተዋል።

በተጨማሪም በሞራል ኃላፊነት (moral duty)ና በህጋዊ ተጠያቂነት (criminal responsibility) መካከል ትልቅ ልዩነት ደግሞ አለ። እንደወንጀል በመሳሰለና በአደጋ ጊዜ ድረሱልኝ ለሚል የግለሰብ ጥሪ እየሰሙ ወይም እያወቁ፣ አለመድረስ በህግ ኃላፊነት አያስጠይቅም፤ አያስቀጣምም። በ1970ዎቹ ውስጥ ኒው ዮርክ ከተማ በወንጀለኛ እጅ ተወግታና ተደብድባ፣ ድረሱልኝ እያለች በምሽት መንገድ ላይ ስትጣራ 12 ያህል ጎረቤቶቿ ሰምተው ሳይደርሱላት ለተገደለችው ወጣት አሜሪካዊ ኪቲ ጂኖቬዜ በህግ የተጠየቀ ሰው የለም። እነዚህ ሰዎች ለሌላ ሰብእ እርዳታ ባለመድረሳቸው በሞራል ኃላፊነት (moral duty) ሊያስጠይቃቸው ቢችልም ቅሉ ህግ ተጠያቂ (criminal responsibility) አያደርጋቸውም። የአሜሪካን ሕግ ለሰው በእርዳታ ባለመድረስ ህጋዊ ተጠያቂነትን እንደፖሊስ፣ የሕክምናና ሶሻል ዎርከርስ ወዘተ ባለሙያዎች ሌላ፣ አንዱ/ዷ ለሌላዋ/ው በህግ ጋብቻ ትዳር (contractual status) በተሳሰሩትና ለህፃናት ተንከባካቢ ለሆኑት ወላጆች (parental responsibility) ላይ ይጥላል። በአደጋ ጊዜ (ለምሳሌ መኪና አደጋ ወይም በወንጀል) ለተጎጂዎች ደራሽ የሆነ ቅን ሰው፤ ተጎጂው ዞሮ እርዳታው እንዲያውም ይበልጥ አካሌን ጎድቶኛል ብሎ በፍትሐብሔር ሕግ እንዳይከሰው፤ በአሜሪካን ውስጥ የሳምራዊ ህግጋት (Good Samartian Laws) የሚባል ተከላካይ ህግ አለ። የዚህም ህግ ዓላማ፣ እርዳታ ሰጭዎች የህግ ክስ በመፍራት ተረጂን ከመርዳት ዘወር እንዳይሉና በሉቃስ ወንጌል እንደተጠቀሰው እንደደጉ ሳምራዊ፣ ሰብአዊ ወይም ምግባረ ሰናይ ግዴታቸውን እንዲወጡ ነው። ዋና ጥያቄው እንግዲህ፣ ምግባራችን እንደሌዋዊው ልበ ደንዳና ወይስ እንደሳምራዊው ባህሪ ምንጊዜም ተቆርቋሪ ይሆናል? ነው።

[20] Mill, J., *On Liberty*, Penguin, New York, 1987, ገፅ 68.

[21] ሎርድ ዴቭሊን ከዚህ አንጻር የሰጡትን አስተያየት እንዲሁም የሀርትን ትንተና በሀርት፣ ገፅ 18-9 ይመልከቱ፡፡

## ለፍትህ ባለሙያዎች ከፍ ያሉ የስነ ምግባር መመዘኛና መመሪያዎች

ከፍ ያለ የስነ ምግባር መመዘኛና መመሪያዎች ለምን ያስፈልጉናል? የሚለው ሌላው አቢይ ጥያቄ ነው። በፍትህ ሙያ ኃላፊነትና ሥልጣን ዘርፍ የሚቀረፁ ውሳኔዎች ወይም የሚወሰዱ እርምጃዎች ለሕዝብ ሰላምና ደህንነት ሲባሉ ሲባሉየሚከናወኑ ናቸው። ይሁንና፣ እነዚህ ውሳኔዎች ደግሞ ያልተጠበቁ መዘዞች ሊኖራቸው ይችላል። ለምሳሌ፣ በፍርድ ሥርአት ውስጥ ንፁሃን እንደጥፋተኞች ሊቀጡ ይችላሉ (wrongful convictions)፤ ወንጀለኞች በነጻ ሊለቀቁ ይችላሉ። ይህም ሲሆን የአሳሪንንና የመርማሪን ፖሊስ እንዲሁም የከሳሽ አቃቤ ህግንና የፈራጅ ዳኛን ውሳኔ በጥቅል ከሞራል ችሎት ፊት ለዳኝነት ያቀርባል። የወንጀል ፍትህ ባለሙያዎች እንደዚህ አይነት የእለት ተእለት ውሳኔዎችና እርምጃዎችን የመውሰድ ሥልጣንና ኃላፊነት አላቸው፤ ይህም አማርጦ የመወሰን ስልጣን (discretion)የሚባለው ነው። እንዲህ አይነቱ በሀላፊነት አማርጦ የመወሰን ሰልጣን፣ ህጋዊ ሥልጣንን ሲገልፅ፣ ከአሉት አማራጮች መካከል (ለምሳሌ፣ ማሰር ወይም አለማሰር፣ መቅጣት ወይም አለመቅጣት ወዘተ) ውስጥ አንደኛው እንደውሳኔ መውሰድ የሚያስችል ነው።

በተጨማሪም፣ በግል ኃላፊነት የሚወሰድ ውሳኔ ከማህበራዊ ኃላፊነት (ማለትም ፍትሃዊነት፣ ግልፅነት፣ ተጠያቂነት፣ ሚዛናዊነት፣ ያለአድልዎ መሥራት ወዘተ) ጋር በጥቅም የስውር ግጭቶች (hidden conflicts) ሊያስከትል ይችላል።ለምሳሌ፣ የዘመድ ሥራ (nepotism) ፣ እጅ መንሻ ተቀብሎ ጉዳይ የማስፈፀም ሙስና፣ ሥልጣንን ያላግባብ መጠቀም፣ በግል ባለመጣጣም ወይም በግል ጥላቻ የአድልዎ ሥራ መፈፀም ወዘተ።

ስለዚህም ነው እንግዲህ፣ አንደኛ፣ በሙያችን ሁልጊዜም በንቃት፣ በአስተዋይነት፣ በተመራማሪነት ስነ ምግባራዊ ትልም ሊኖረን የሚገባው። እንደፈላስፋው ዘርዓ ያቆብ አገላለፅ፣ ብርሃነ ኅሊና ሊኖረን የሚገባው። ሁለተኛም፣ የመንግሥት ተሿሚዎችና ተመራጮች በተለይም የወንጀል ፍትህ ባለሙያዎች ከሌላው ሕዝብ በተለየ ከፍ ባለ የስነ ምግባር መመዘኛ ወይም መለኪያ አንፃር (ሙያዊ የስነ ምግባር ደንብ) ይመዘናሉ። ምክንያቱም፣ ከሌላው ተራ ዜጋ የተለየ ህጋዊ ሥልጣን ወይም ኃይል ስላላቸው ነው፤ ውሳኔያቸውና እርምጃቸው በግለሰቦች ሕይወትና በህብረተሰቡ ላይ ቀና ውጤትም ሆነ የከፋ መዘዝ ስለሚኖረው ነው። ይህንንም ደግሞ የላቀ መመዘኛ መቀበል ወይም ስነ ምግባራዊ ምሳሌነትን መሸከም እንደፈተና ሳይሆን እንደክብርም ማየት መቻል አለባቸው።

የወንጀል ፍትህ ሥርዓት ሙያተኞች ስነ ምግባር መመሪያዎች፣ በብዙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ የትምህርትና የግል ተቋሞች ውስጥም ማስታወቂያ ሰሌዳዎች እነዚህን ደንቦች አካትተው ያስገነዝባሉ። በርግጥም እንደሚጠበቀው የዚህ ሁሉ መጨረሻ ግብ እነዚህን አጢኖ በተግባር የማዋሉጉዳይ ነው፤ ባህሪአችን ውስጥ እንዲሰርፁና የእለት ግብረ ገባዊ ገፅታዎቻችን እንዲሆኑ በትጋት ዘወትር የማሰቡ ጉዳይ ነው። የሙያተኞች ስነ ምግባር ደንቦች በየንዑስ ዘርፎቻቸው እንደየሙያ ክፍላቸው እንደኢትዮጵያ ሁሉ በሌሎችም አገሮች ተጽፈው ተደንግገዋል። ለዳኞች፣ ለፖሊሶች፣ ለዓቃቤ ህጎች፣ ለጠበቆችና ለማረሚያ ቤት አስተዳደርና ስታፍ፣ በሃገር በአህጉርና በአለም አቀፍ ደረጃዎች ተረቀዋል። እነዚህም ባጠቃላይ ሰብአዊ ክብርን፣ ፍትሃዊነትን፣ ተጠያቂነትን፣ ግልፅነትንና ተደራሽነትን ያካትታሉ። ከብዙዎቹ በጥቂቱ ሲዘረዘሩ፡- የሰው ልጅ ሰብአዊ ክብርን መንከባከብ፣ አስፈላጊ ኃይል ብቻ በአግባቡ መጠቀም፣ ተገቢ ምሥጢር መጠበቅ (confidentiality)፣ የአካልና የአእምሮ ሥቃይ ከሚያደርሱ እርምጃዎች (torture) መታቀብ፣ በቁጥጥር ስር ያሉ ተጠርጣሪዎች ተከሳሾችንና የፍርድ እስረኞችን ደህንነት መንከባከብ፣ ከሙስና መፅዳት፣ የህግ የበላይነትን ማክበርና እነዚህን ስነ ምግባራዊ ደንቦች መከተልና ሙስናን በይፋ ማጋለጥ ናቸው።

ለፌዴራል ዐቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ የወጣው ደንብ፣[22] ስለሃቀኝነትና ቅንነት፤ "የሰዎችን ክብርና ሰብአዊ መብት" ስለመንከባከብ፤ ስለሙያ ክብርና ምስጢርን መጠብቅ ይዘረዝራል። እንዲሁም፣ ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የስነ ምግባር ደንብም፣[23] "የሙያ ሃላፊነትን በቅንነት፣ በታማኝነት እና በእውነተኛነት መወጣት" እንደሚያስፈለግ ያስገነዝባል። በተመሳሳይም፣ የክልል አስተዳደሮች የዳኞች ስነ ምግባርና ዲሲፕሊን ደንብ፤ ሙያዊ ንፅሕናን፣ ግልፅነትን፣ ታማኝነትን፣ ቅንነትን፣ተጠያቂነትን፣ አድልዎ አለመፈፀምንና የሕዝብ አገልጋይነትን ያስገነዝባል።[24] እነዚህና ሌሎች ተመሳሳይ ደንቦች፣ ለሚፈፀሙ የስነ ምግባር ጥፋቶችና ወንጀሎች የዲሲፕሊን እርምጃዎችና ቅጣቶችን ዘርዝረው ያስጠነቅቃሉ።[25] የስነ ምግባር መሰረታዊ መርሆዎችንም በዝርዝርና በግልፅ ያትታሉ።[26]

እነዚህን የስነ ምግባር ደንቦች በየዘርፉ በህግ ለማስፈፀም አዳጋች ነው። ይሁንና ሙስናን ለመቋቋም የፌዴራል ስነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያና የስነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ (1997 ዓ.ም.)፣ እንዲሁም የስነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች አሠራርን ለመወሰን የወጣ ደንብ (2000 ዓ.ም.) ለዚሁ ችግር በህግ አስፈጻሚነት የታቀዱ መልካም ጅምሮች ናቸው። ከዚሁም ጋር ለፌዴራል ባለሙያተኞች የተዘጋጀው የስነ ምግባር ማሰልጠኛ ፕሮግራምም አለ። እነዚህ ሁሉ ጥረቶች የሚደገፉ ናቸው። በአንድ በኩል፣ ቢያንስ ሙያተኞችን ስለስነምግባርና ኃላፊነታቸው እንዲሰማቸው (sensitize) ያደርጋቸዋል። በሌላው ጎን፣ ይህ ለቋሚና ዘለቄታዊ ትኩረት መልካም ጅማሪም ነው።

### *የስነ ምግባር ምህዳር*

በሙያዊ ኃላፊነታችን የምርምራችን ትኩረት፣ በድርጊቶቻችን ትክክለኛነትና ስህተት፣ በድርጊቶቻችን መልካም ውጤቶችና ጎጂ መዘዞችን፣ በሰብዓዊ ባህሪና በጎ ምግባር፣ በዝንባሌ ወይም አዝማሚያና በጎ ፈቃደኝነት (good will)፣ ውሳኔያችንን በስሜት ላይ ሳይሆን በተገቢ ልቡናዊ ግንዛቤ(good reason) ላይ እንዲያርፍ ማስቻል ነው። በዚህም አኳያ፣ አመለካከታችን እንዳይጠብ፣ የማንስማማባቸው የሚመስሉንን ሃሳቦችንም እንኳን መመርምር ተገቢ ነው። ምክንያቱም የሃሳባችንን ውሱንነት ብዙ ጊዜ ለራሳችን ግልፅ ላይሆኑ ይችላሉና። ማየት የምንችላቸው ጉዳዮች ሊሰወሩብን ይችላሉ። በአንፃሩ ሌሎች በቀላሉ ይገነዘቡታል። ቀናናዊ ባለመሆን

---

[22] "ስለፌዴራል ዐቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ"፣ ቁጥር 44/1991፤ *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ*፣ 5ኛ አመት፣ ቁ.8፣ አዲስ አበባ፣ ህዳር 11 ቀን፣ 1991 ዓ.ም.

[23] "ስለ ፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች የስነምግባር ደንብ" የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ፣ ቁጥር 57/1992፤ *ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ*፣ 5ኛ አመት፣ ቁ.8፣ አዲስአበባ፣ ህዳር 11ቀን፣ 1991 ዓ.ም.

[24] "የአማራ ክልል ፍርድ ቤት ዳኞች ስነ ምግባርና ዲሲፕሊን ደንብ"፤ የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት፤ *ዝክረ ሕግ*፤ 7ኛ አመት፣ ቁጥር 24፤ ባሕር ዳር ነሐሴ 5፣ 1994 ዓ.ም.

[25] *ስነ ምግባር እና ሙስና (የግንዛቤ ማስጨበጫ ጽሁፍ)* ፤ የፌዴራል የስነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን፤ 2001.

[26] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 99-103.

አእምሮቻችንን ለእርማትና ለአዲስ እውቀት ክፍት እናድርግ። ቆምና መለስ እያልን ምግባራችንና ተግባራችንን እናጢን። በስራችንና ውሳኔአችን ላይ ሁሉ ጤናማ ጥርጣሬ ይኑረን። ለእርማት ይመቸናልና። ስራችንንና ውሳኔያችንን በጥናትና በመረጃ ከመደገፍ ይልቅ በግምትና በመላ ምት አናካሂድ። ሃሳባችንን የማይደግፉ የሚመስሉንን ነገር ግን ጠቃሚ መረጃዎች አናጣጥል። ሰዎችን በማንነታቸው (በፆታ፣ በብሔር፣ በማህበራዊ መደብ፣ በእድሜ) መሠረት በሌለው ጥላቻ አይን አንመልከት። ሁለት ስህተቶች አንድ ትክክለኛ ነገር እንደማያስከትሉ እንገንዘብ።

ስነ ምግባራችን በፀና ውሳጣዊ ግብረ ገባዊ እሴት (intrinsic values) ላይ ይቁም። ጂይ አልባኒስ[27]፣ "ሌሎች አዩን አላዩን፤ ተከታተሉን አልተከታተሉን በጎ ምግባር ሊኖረን ብቁ ነን ወይ?" ያለው ይህንኑ ከራስ የፈለቀ ስነ ምግባራዊ ብቃት የሚያስረዳ ነው። ለየሁኔታው አግባብ ያለው ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት ዝግጁ ነን ወይስ አይደለንም? በሃላፊነታችን የሚጠበቅብን ስነ ምግባራዊ ገዴታ ምንድን ን ነው? ህጉና የፖሊሲ መመሪያዎች የሚጠይቁት ምንድን ነው? ለዚህ ሁሉ ዝግጅታችን ደግሞ፣በውጫዊ ቅጣት ፍርሃት ወይም ማበረታቻ ሽልማት (extrinsic values) ብቻ የቆመ ስነ ምግባር ፅኑ መሠረት አይኖረውም። በቅጣት ፍርሃት ብቻ የሚታነፅ በጎ ምግባር ጽናትና ዘለቄታ የለውም። እንዲያውም ተደረሰብኝ፤ አልተደረሰብኝም አይነት የድመትና አይጥ ድብብቆሽ ጨዋታ ነው የሚሆነው። እራሳችንን (ምግባራችንን) በቅጡ እናውቃለን ብለን አንሳሳ፣ ስለዚህም ያልተቋረጠ የግል ምርምር እናድርግ። የግብረ ገባዊ የግል ምርምር ስናደርግ ደግሞ፣ የስነ ምግባር ንድፈ ሃሳቦች (ethical theories) ፈለግ ያሲዙናል።

## *የስነ ምግባር ዋና ዋና ንድፈ ሃሳባዊ አመለካከቶች*

የስነ ምግባራችን ምርምር መመዘኛ ወይም መለኪያ ከሆኑት መካከል ስድስቱን የስነ ምግባር ክፍሎች ያካደኑት ንድፈ ሃሳቦች፡- 1) ማህበራዊ ውል (Social Contractualism)፣ 2) የተጠቃሚነት ምግባርና ገቢር (Utilitarian Ethics)፣ 3) ግዴታዊ ስነ ምግባር (Deontology)፣ 4) ምግባረ ሰናይ (Ethics of Virtue)፣ 5) አንስታይ ስነ ምግባር (feminist ethics) እና 6) ፍትሃዊ ህሊና(Sense of Justice) ናቸው። እነዚህም ንድፈ ሃሳቦች፣ ከላይ በተዘረዘሩት *በቢሆን ስነ ምግባር* (Normative ethics) እና *በልዕለ ስነ ምግባር* (Metaethics) ውስጥ ይጠቃለላሉ።

1ኛ፣ ማህበራዊ ውል (Social Contractualism)

ከፍፁም ግላዊ ጥቅም ይልቅ ለጋራ ጥቅምና ለማህበራዊ ኑሮ ትኩረት የሚሰጥ ንድፈ ሃሳብ ነው። ይህም ማለት ግን የግል ፍላጎትንና ጥቅምን ፈጽሞ መሻር ማለት አይደለም። ወይም ደግሞ እንደ ስቶይኪስቶች "ምን ቸገረኝነት" ወይም ስነ ምግባራዊ ግለኝነት (ethical egoism)፣ "ከራስ በላይ ነፋስ" አይነት አፅናፋዊ ግለኝነትም በማህበራዊ ሕይወት ውስጥ ሥፍራ የለውም። የማህበራዊ ውል አስተሳሰብ ግለሰቦች ተሰባስበው፣ ተከባብረውና ተቻችለው ለራሳቸው የግል ጥቅምና ደህንነት ጭምር፣ በጥቅል እንደህብረተሰብ በአንድ መንግሥትና በጋራ ሕግ ስር የሚኖሩበት ስርዓት ነው።

[27] አልባኒስ፣ ገፅ 139.

የማህበራዊ ውል፣ ሰዎች በግለኝነት ማለቂያ በሌለው የግለሰብ ጎጂ ግጭት (ቶማስ ሀብስ፣ የተፈጥሮዊ ሁነት - state of nature የሚለው) ግለሰቦችን እንደ አንድ አካል (body politic) የሚያዋህድ ፖለቲካዊ ዘይቤ ነው። በዚህም ማህበራዊ ውል ፅንስ ሀሳብ የተነሳ፣ ወንጀል ሲሰራ ተጎጂው ግለሰቡ ወይም የቅርብ ቤተሰቡ ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ ህብረተሰቡ በመሆኑ መንግሥት አጥፊውን ከሶ ያስቀጣዋል። ከዚህ በሚመነጨው ህጋዊ ፍልስፍና፣ ወንጀለኛውም በህብረተሰቡ ስም በመንግሥት የሚቀጣው፣ ከሌሎች ዜጎች ጋር በሰላም ተቻችሎ ለመኖር የገባውን ማህበራዊ ውል በመጣሱ ነው።

2ኛ፣ በተጠቃሚነት ምግባርና ገቢር (Utilitarian Ethics) ንድፈ ሃሳብ

እንደመንደርደርያ የሰው ልጆች ወይ ደስታን ወይ ስቃይን ሊያስከትሉ የሚችሉ ምርጫዎችን አመዛዝነው መፈፀም የሚያስችል አእምሮአዊ ብቃት (rationality) አላቸው ብሎ ይነሳል። አያይዞም፣ ማንኛውም በግል የሚወሰን ውሳኔና የሚፈፀም ተግባር፣ ውጤቱ በአመዛኙ ደስታንና ፍላጎትን የሚያረካ መሆን አለመሆኑ፣ ውጤት ለብዙኃኑ ደስታ ማምጣት አለማምጣቱ፤ እስካመጣ ድረስ ደግሞ ይህንኑ በቀዳሚነት መሻት ተገቢ የስነ ምግባር መለኪያ እንደሆነ ያረጋግጣል። ሰዎች በመሠረቱ በባህሪአቸው ደስታን ፈላጊዎች እንደሆኑና ስቃይን የማይሹ መሆናቸውን ይገልፃል። የዚህ ሃሳብ አመንጭ ከሆኑት መካከል እንግሊዛዊውያኑ ፈላስፋዎች ጀረሚ ቤንታም ና ጃን ስቱዋርት ሚል፣የተጠቃሚነት መርህ (priniciple of utility) አንድ ውሳኔ ወይም ድርጊት፣ "ባብላጫው ደስታን ለአብዛኛው ለሚመለከተው ሕዝብ ጥቅም መሻት ተገቢ ነው" ይላሉ።[28]

በዚህም አስተሳሰብ የአንድ ድርጊት ወይም ውሳኔ መልካም ስነ ምግባራዊነት የሚለካው በሚያስከትለው የተጠቃሚነት ውጤት ነው። ለሌሎች በርካታ ሰዎች ጥቅምና ደስታ ሲባል የአንድ ወይም የጥቂቶች መብት ቢጣስ ይመረጣል። ለምሳሌ፣ በሕዝብ ላይ አደጋ ለማድረስ በተደረገ የምሥጢር ሴራ ላይ የተሳተፈ ተጠርጣሪ ቢያዝና ምስጢሩን እንዲያወጣ በአካል ስቃይ (torture) ቢመረመር፤ ውጤቱ ሕዝብን ከጥቃት ለመጠበቅ እስከሆነ ድረስ (በተለይ ገቢራዊ ተጠቃሚነት - አክት ዩቲሊቴርያን ንድፈ ሀሳብ አንፃር) ድርጊቱ የሚደገፍ ይሆናል። ሌላም ምሳሌ ለማንሳት፤ አንድ ሰው ላይ የሕይወት አደጋ እንዳይደርስ ሰውየውን ደብቆ፣ አላየሁትም ብሎ መዋሸትና እንደዚህ አይነት ውሸት በዚህ ንድፈ ሃሳብ ተደጋፊ ይሆናል። ባጭሩ ውጤቱ ጠቀሜታ እስካለው፤ መንስኤው (መነሻው) አጠያያቂ አይሆንም። ይህም በእንግሊዝኛ፣ "the end justifies the means" የሚለው አገላለፀ ነው። በአገራችን፣ "የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው" እንደሚለው አባባል አይነት።

3ኛ፣ ግዴታዊ ስነ ምግባር (Deontology)

በ18ኛው ክፍለ ዘመን የጀርመን ፈላስፋ ኢማኑኤል ካንት እንደ ስነ ምግባራዊ ንድፈ ሃሳብ፣ "የግብረ ገብነት መንደርደሪያ" (Groundwork of the metaphysics of morals) በሚል ርእስ የነደፈው ነው። ከዚህ ንድፈ ሃሳብ አንፃር፣ ግብረ ሠናይ ስራዎችን ከላቀና ሁለንተናዊ መርሆ አኳያ

[28] ባንክስ፣ ገፅ 274.

ብቻ መሥራት ግዴታ እንደሆነና ተገቢነት እንዳለው በአፅናኦት የሚያስገነዝብ ነው። ዲኦንቶሎጂ የሚለው ቃል ከግሪክ *ዲኦን* ከሚለው የመነጨና ትርጉሙም ግዴታ ማለት ነው።

ለካንት፣ የአንድ ግለሰብ ውሳኔ ወይም እርምጃ በጎነት የሚለካው ከሚያመጣው የደስታ ውጤት አኳያ ሳይሆን መርህን ተከትሎ በመሠራቱ ብቻ ነው። ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ ማንኛውንም አይነት መልካም ነገር ለማድረግ፣ በቅድሚያ በጎ ፈቃድ (good will) ሊኖራቸው ይገባል፤ የድርጊታቸውም በጎነት መመዘኛም ከዚሁ በጎ ፈቃዳቸው ይመነጫል።[29] የባህሪ ጥንካሬ፣ ታታሪነት፣ ድፍረት፣ ፅናትና ታማኝነት የመሳሰሉት በራሳቸው (ያለበጎ ፈቃድ) ለብቻቸው ምግባረ ሰናይነትን አይገልፁም። እንዲያውም፣ ያለበጎ ፈቃድ ጠንክረው፣ በድፍረትና በፅናት የሠሩት ስራ ጎጂም ሊሆን ይችላል፤ የከፋ ጉዳትና መዘዝ ሊያስከትል ይችላል።[30] ስለዚህም፣ ጥንካሬያችን፣ ድፍረታችን፣ ፅናታችን፣ ታታሪነታችንና ታማኝነታችን ሁሉ በበጎ ፈቃድ መገራት አለባቸው። በጎ ፈቃድ ደግሞ፣ በሚያስከትለው ውጤት ወይም ጠቀሜታ አይደለም ሰናይነቱ የሚለካው፤ ስለራሱ በራሱ የላቀ እሴት እንዳለው ሆኖ እንጂ።[31] እንዴት ያለፍሬያማ ውጤት የሚሠራ ሥራ በጎነቱ ይለካል? ይህ ሃሳብ የማይጨበጥ ብቻ ሳይሆን እንደቅዠትም ሆኖ ሊታይ ይችላል። ይሁንና የሰው ልጆች ድርጊት ለጥቅም እንደሆነ ብቻ አድርጎ ማሰብና ከዚህም ጥቅማ ጥቅም ብቻ ደስታ እንደሚገኝ አድርጎ ማሰብ፤ (እንደካንት አገላለፅ) ትልቅ ክብር የሚሰጠውን የሰብአዊ ኅሊናዊ ብቃት ግምት ውስጥ ያስገባል።[32] (ከፍትፍቱ ፊቱ የሚለው የሀገራችን አባባል በመጠኑም ይህንን ሊያስገነዝብ ይችላል) ። ካንት አያይዞም፣ የሰው ልጆች የደስታ ምንጭ በበጎ ፈቃድ መሠረት ላይ በላቀ ስነ ምግባራዊ መርሆ ሕይወታቸውን መምራት ነው ይላል።[33] የዚህም በጎ ፈቃድ መርሆ ግዴታ (duty) ነው።

*ሥራችንን ሁል ጊዜ በበጎ ፈቃድ ለመሥራት* ግዴታዊ (from duty) *መሆን የሚገባው* እንጂ፤ ከግዴታ ጋር እንደሚጣጣም (in conformity with duty) ሆኖ አይደለም።[34] ለዚህ ካንት የሰጠው ቀላል ምሳሌ፣ "ጎረቤትህን እንደራስህ አፍቅር" የሚለውን የመፅሐፍ ቅዱስ ግብረ ገባዊ ቃል ነው። ይህንን ቃል ለመቀበልና ለማክበር፣ እንደግዴታዊ መርሆ ሆኖ እንጂ፣ በስሜታዊ መልኩ አይደለም። ይህንን የካንት ምሳሌያዊ ሃሳብ ላብራራ። በአንድ በኩል፣ ስሜታችን ተለዋዋጭ የመሆኑን ያህል፤ ደስ ያለን ቀን ጎረቤት አፍቃሪዎች፤ የከፋን ቀን ደግሞ ለጎረቤት ጥላቻ ልናሳይ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ይህ ጎረቤትን የማፍቀር ግዴታዊ መርሆ፣ በጎረቤቶቻችን ጠባይ ምንነት የሚወሰን አይደለም። ክፋት ሲያሳዩን ክፉ ከሆንን፤ ምግባራችን በራሳችን ፅኑና የላቀ መርሆ ላይ ከመቆም ይልቅ በሌሎች ጠባይ ሊዋልል ነው። እንዲያውም፣ የእኛ ፅኑና የላቀ ግዴታዊ መርሆ ለጎረቤቶቻችን ምግባር አርአያ ቢሆን ይመረጣል።

[29] Kant, I., *Groundwork of the Metaphysics of Morals*, Cambridge University Press, Cambridge, 1998 ፣ ገፅ 7[Hereinafter ካንት].

[30] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 7.

[31] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 8.

[32] ዝኒ ከማሁ

[33] ዝኒ ከማሁ

[34] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 11.

የአንድ ሰው የዕለት ተዕለት ተግባርና ውሳኔ ሁለንተናዊ ሕግ (universal law) ሆኖ መታየት ይገባዋል።[35] ለምሳሌ፣ የገቡትን ቃልን መጠበቅ ማለት ለሌሎች ሁሉንተናዊ አርአያ መሆን ማለት ነው። አለበለዚያ፣ የገባሁትን ቃል ግዴታዬ ነው ብዬ ካልጠበቅሁ፣ ሌሎችም እንደዚሁ ቃላቸውን የማይጠብቁ ይሆናሉ። ውሸት ያዋጣል፤ ይጠቅማል ካልንም፣ ሁለንተናዊ የዋሾዎች ማኅበረሰብ ልንቆረቁር ነው። ሌላው ምሳሌ፣ የራስን ህይወት ማጥፋት (suicide) ማለት በአሉታዊ አርአያነት ክቡር የሆነውን የሰውን ልጅ ህይወት ማጣጣልና ለሌሎችም አጉል አርአያ መሆን ማለት ነው። ስለዚህም ነው ካንት፤ በአንድ በኩል፣ ማንም ግለሰብ ድርጊቱ ወይም ውሳኔየ ይህ ይሆናል ሲል፤ ይህ በአርአያነት ለሌችም ሁለንተናዊ ህግ (universal law) እንደሚሆን መገንዘብ ግዴታው ነው ያለው።[36] በተመሳሳይም፣ አድራጊው ግለሰብ ራሱን ሁለንተናዊ ህግ አርቃቂ (universal law-giver) አድርጎ መቁጠር አለበት። በዚህም አይነት ግዴታዊ መርሆ ደግሞ፣ ካንት እንደሚያስገነዝበው፣ ሰዎች "የጋራ ሰብአዊ ልቡና" (common human reason) ይጎናፀፋሉ።[37]

የካንት ቀዳሚና ሁለንተናዊ መርሆ ደግሞ፣ የማያሻማ የልቡና መመሪያ ወይም ቀመር (categorical imperative) የሚላቸው ናቸው።[38] በዚህም መመሪያ መሠረት፣ ድርጊቶቻችን ወይም ውሳኔዎቻችን ሁሉ ለሚያስከትሉት ጥቅም ሳይሆን፤ ለስነ ምግባራዊ መርሆ ሲባል ብቻ መፈጸማቸው የግድ ነው። ለምሳሌ፣ ለተቸገረ ሰው ችሮታ ስንሰጥ ለመርዳት ካለን ሰብአዊ ግዴታ ነው። የመንፈስ ደስታ እንዲሰጠን ከሆነ፣ ካንት እንደምግባረ ሰናይ አይቀበለውም። በተመሳሳይ፣ እንደፍትህ ባለሙያ ኃላፊዎችየወንጀል ተጎጂዎችን መርዳት ካለብን ከግዴታዊ መርሆ አንፃር እንጂ ለሹመት ወይም ለምስጋና ከሆነ፤ ይህንን የግዴታዊ ስነ ምግባር መመዘኛ አያሟሉም። ይህም የካንት ግዴታዊ ስነ ምግባር፣ ከፍ ብለን ከተመለከትነው ቤንታማይት የጠቀሜታ ስነ ምግባር (utilitarian ethics) ጋር መለየት ብቻ ሳይሆን ይጋጫልም። ለሆነ ውጤት ወይም ጥቅም ፍለጋ የሚሠራ ሥራን፣ ካንት መላ ምታዊ መመሪያ (hypothetical imperative) ይለዋል። ለምሳሌ፣ ውሸት ፍሬያማ ውጤት ቢያስከትልም እንኳን በጎ ምግባር አይደለም። ለካንት፣ አለመዋሸትን በራሱ (ምን ውጤት ይኑረው አይኑረው) እንደስነ ምግባር ደንብ መከተል የሁሉም ሰው ግዴታ ነው። በተመሳሳይ፣ ለብዙኃኑ ደህንነት ወይም ጥቅም አንድን ግለሰብ ወይም ጥቂቶችን መስዋእት ወይም መጠቀሚያ (ለህዝብ ደህንነት ሲባል በወንጀል ተጠርጣሪ ላይ የአካል ስቃይ ምርመራ) ማድረግ ተገቢ አይደለም። ካንት ለእያንዳንዱ ግለሰብ የላቀ ሰብአዊ ክብር ወይም ሉዓላዊነት ያረጋግጣል፤ ይህንንም kingdom of ends ይለዋል።[39]

[35] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 15.

[36] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 30.

[37] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 18.

[38] ዝኒ ከማሁ፣ገፅ 25.

[39] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 41-2.

4ኛ፣ የአሪስጣጣሊስ ምግባረ ሰናይ (Ethics of Virtue)

ምን አይነት ሰው ነው መሆን ያለብኝ? ምንስ አይነት በጎ ምግባር ሊኖረኝ ይገባል? ለመሳሰሉት ዋና ዋና ስነ ምግባራዊ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል። ከክርስቶስ ልደት በፊት በአራት መቶ አመት የኖረው የጥንታዊ ግሪክ ፈላስፋ አሪስጣጣሊስ በልጁ ስም የሰየመው የስነ ምግባር ፍልስፍና “ኒቆሜቀሳዊ ስነ ምግባር” (Nocomachean ethics) በሚል ርእስ ተፅፏል። ለአሪስጣጣሊስ፣ የሰው ልጅ በሕይወቱ ቀዳሚውና የላቀው ዓላማ ደስታን መሻትና መልካም ኑሮን መኖር ነው።[40] ከዚሁ ጋር ተያይዞም ደስተኛ ሰው በግብሩ ቀልጣፋ የሆነና መልካም ኑሮን የሚኖር ነው። ለአሪስጣጣሊስ፣ የምግባረ ሰናይነት መመዘኛው ድርጊትና ልማድ ነው።[41] በጎ ምግባርን በየእለቱ በተግባርና በልምድ ማዳበር ይቻላል ባይ ነው። እንደእርሱ አባባል የተሟላ ምግባረ ሰናይ ለመጎናፀፍ ቋሚ ጥረትን ይጠይቃል። ግብር ምግባርን ይገልጣል፤ ያንፃል። ለማንኛውም የሰው ልጅ፣ የሚያስመሰግነው ወይም የሚያስነቅፈው መመዘኛ ግብሩ ነው፤ አውቆ የሚሠራው ሥራ ነው።[42]

ከስነ ምግባር ምሳሌዎች መካከል ጥቂቶቹ፥ ብልህነት፣ አስተዋይነት፣ ለጋስነት፣ ድፍረት፣ ቁጥብነት፣ ታማኝነት፣ ታታሪነት፣ ቅንነት፣ ደግነት፣ ርኅሩህነት፣ ሃቀኝነት፤ ፍትሃዊነት፣ ራስ-ገዝነት ወዘተ ናቸው። ፍትሃዊ ድርጊት የምግባረ ሰናይ አንድ ዘርፍ ሳይሆን፤ በጥቅሉ እንዳለ ምግባረ ሰናይ ነው።[43] ለአሪስጣጣሊስ፣ ፍትሕ ማለት ለሕግ በግዳጅ ሳይሆን በፈቃደኝነት ታዛዥ ሲሆንና ሚዛናዊ ባህሪ ሲኖር ነው።[44]

ይሁንና፣ ውሳኔያችንና ድርጊታችን ሁልጊዜም ወርቃማውን ሚዛን (Golden Mean) መጠበቅ አለበት።[45] ለምሳሌ፦ በፈሪነትና በጀብደኝነት መካከል ደፋርነትን፤ በስስታምነትና በአባካኝነት መካከል ደግነትን፤ በሰፍሳፋነትና በግዴለሽነት መካከል ጠንቃቃነትን፤ በችኩልነትና በአዝጋሚነት መካከል ቀልጣፋነትን፤ በስንፍናና በቀዝቃዣነት መካከል ታታሪነትን፤ በከሀዲነትና በተለማማጭነት መካከል ታማኝነትን፤ በጉረኛነትና በፈዛዛነት መካከል ትሁትነትን፤ በጅልነትና በመመፃደቅ መካከል አስተዋይነትን፤ በግልፍተኝነትና በቀለስላሳነት መካከል ቁጥብነትን፤ ወዘተ በጥቂቱ በአስረጅነት የሚቀርቡ ሚዛናዊ በጎ ምግባሮች ናቸው።

5ኛ፣ አንስታይ ስነ ምግባር (Feminist ethics)

የሴቶችን በፆታዊ ማንነታቸውና ልዩ ማህበራዊ ልምዶቻቸው ያካበቱትን እውቀትና ችሎታ በማጥናት፤ ከግለኝነት ወደ ኃላፊነት መውሰድ፣ በጎ ምግባር ማለት የግል መስዋእትነትን መክፈል

[40] Aristotle, ‘Nicomachean ethics’ *in* Aristotle: On man in the universe, Walter Black, New York, 1943, pp.85-243፣ ገፅ 92.

[41] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 101.

[42] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 113.

[43] ዝኒ ከማሁ፣ገፅ 158.

[44] ዝኒ ከማሁ፣ገፅ 156.

[45] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 110 – 13.

እንደሆነና ለራስና ለሌሎች ማሰብን የመሳሰሉ ባህሪያዊ ገፅታዎች የሚያካትት ነው።[46] ይህም አንስታይ ስነ ምግባር ጠቅለል ባለ ይዘቱ፣ የእንክብካቤ ስነ ምግባር (ethic of care) ይባላል።[47] የእንክብካቤ ስነ ምግባር፣ ለልጆች፣ ለቤተሰብና ለወዳጆች ሴቶች ባላቸው የቅርብ ግንኙነት የዳበረ መተሳሰብን ይገልፃል። ማህበራዊ ግንኙነቶች በመተሳሰብና በመፈቃቀር ጠበቅ እንዲሉ ይረዳል። ቤተሰብ የማህበራዊ አስኳል የሆነውን ያህል፣ የሴቶች ድርሻና ሃላፊነት በየትኛውም ህብረተሰብ ውስጥ እጅግ ከፍተኛ መሆኑ አያጠያይቅም። በእናትነት፣ በአክስትነት፣ በአያትነትና በእህትነት ሴቶች ለህፃናት እድገትና እንክብካቤ አቢይ አስተዋፃኦና ቀዳሚ ድርሻ አላቸው። የአንስታይ ስነ ምግባር ንድፈ ሃሳብ፣ በሌሎቹ ንድፈ ሃሳቦች ላይ ያላት ሂስ፣ እውቀት በረቂቅ ፅንሰ ሃሳቦች ብቻ እንደሚገለጡ አድርገው ማቅረባቸውንናበአንድምታ ሴቶች ("ስሜታዊ" እንጂ) ለዚህ አይነት ጥልቅ ፍልስፍናዊ እውቀት እንደወንዶች "ብቃት" የላቸውም በሚል የተሳሳተና የተዛባ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ነው። እንዲያውም፣ በአንድ በኩል፣ ሴቶች በተመደበላቸውና በያዙት ማህበራዊ ሰፍራ፣ ከራሳቸው የግል ጥቅም አልፈው ሌሎችን ማሰብናመንከባከብ አጠቃላይ ባህሪአቸው ነው። በተጨማሪም፣ በታሪካዊና ማህበራዊ የፆታ አድልዎ ስር በመኖራቸው፣ ከማንም በላይ ስለፍትህ፣ ርትእና እኩልነት ተቆርቋሪ ናቸው። በዚህም የበለፀገ ማህበራዊ ልምዳቸው ለየትና ላቅ ያለ የተንከባካቢነት ሰነ ምግባር ተጎናፅፈዋል።

6ኛ፣ የጃን ራውልስ ፍትሃዊ ህሊና (Sense of Justice)

ፍትሃዊነትን በየእለት እለት ህይወታችን ውስጥ በኅሊናችን ውስጥ መቅረፅ ወይም ማዋሃድ አለብን ከሚል መንደርደሪያ ሃሳብ ላይ በመነሳት፣ ራውልስ "የፍትህ ንድፈ ሃሳብ" (theory of Justice) በሚለው መፅሐፉ ውስጥ፤ "የዴሞክራቲክ ህብረተሰብ መዋቅራዊ መሠረቱ ፍትህ (justice) ነው" ይላል።[48] አያይዞም፣ ፍትህ ዋናና ቀዳሚ የማኅበራዊ ተቋሞች ፀጋ ነው ይላል።[49] የፍትህ ጥንድ መርሆዎችየሚባሉት፤ አንደኛ፣ የሰዎች የእኩልነት መብትና ነፃነት መከበርና፤ ሁለተኛ፣ የሀብትና የገቢ ምንጮች (primary social goods) ለሁሉም የመዳረስ ጉዳይ ነው።[50] እነዚህ ማኅበራዊ ሀብቶች እንደ የስራ፤ ትምህርት፣ ጤና አገልግሎት፣ ወዘተ ናቸው። ይሁንና፣ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ማህበራዊ እኩልነት የተዛባ ቢሆን እንኳን እጅግ የተጎዱ ማህበራዊ ክፍሎችን እስከተንከባከበ ድረስ የሚደገፍ ማኅበራዊ ሥራዓት ነው ይላል።[51]

እኩልነትም የፍትህ ዋነኛው መመዘኛ ወይም መለኪያ ሲሆን፤ የማኅበራዊ ፍትህ መርሆም ዜጎች የሚጎናፀፏቸው መብቶችና ግዴታዎች ነው።[52] በግልባጩም፣ መልካም ህብረተሰብ የተዛባ

---

[46] ጊሊጋን ፣ ገፅ 19.

[47] ባንክስ፣ ገፅ 324.

[48] Rawls, J., *A Theory of Justice*, Harvard University Press, Cambridge, 1971፣ ገፅ viii.

[49] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 3.

[50] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 60-1.

[51] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 75)

[52] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 4.

እኩልነትን መግታት የሚችል ነው። ማኅበራዊ ተቋሞችም ፍትሃዊ የሚያሰኛቸው ለማህበረሰቡ በጎ ህልውና በሚያደርጉት እንክብካቤና አገልግሎት ነው።[53] ራውልስ፣ ደጋግሞ የሚያነሳቸው ጥያቄዎቹ፡- ፍትሃዊና ሚዛናዊ ህጎች አሉ ወይ? በእኩልነት ላይ የቆመ ፍትሃዊ ሥርዓት አለ ወይ? ፍትህና ርትዕ በቀዳሚ ሥፍራ ላይ (original position) ሰዎች ለተሟላ እኩልነት ሲሉ (ለጥቅማቸው እንዳያዳሉ ማኅበራዊ ማንነታቸውንና የሀብት ይዞታቸውን ሳያውቁ ተጋርደው - veil of ignorance) የሚጎናፀፉት ነው በሚል በማይዳሰስ መላ ምታዊ (hypothetical) ሃሳብ ያቀርባል።[54] የጆን ራውልስ ንድፈ ሃሳብ ከፍ ባለ ደረጃ ማኅበራዊና መንግሥታዊ ፖሊሲዎችን ስለሚመለከት፤ ባማዛኙ የስነ ምግባራዊ ጉዳዮች (ethical issues) ለመፍታት የሚጠቅም ነው።

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን የስነ ምግባር ንድፈ ሃሳቦች መሠረት አድርጎ በእለት ኑሮም ውስጥ ሆነ በሙያ ኃላፊነት ላይ፤ የሚያጋጥሙ የስነ ምግባር አጣብቂኞችን (ethical dilemmas) ለመፍታት የሚያስችል የገቢራዊ ስነ ምግባር (applied ethics) ቀመር የሚከተለውን ይመስላል[55]፡-

1) አጣብቂኙ በምን መልክ ተከስቷል?
2) የተከሰተበት ሁኔታና የመረጃ ዝርዝሮች የትኞቹ ናቸው?
3) ለመፍትሄ የሚቀርበው ውሳኔ በምን መረጃ ላይ ይደገፋል?
4) መፍትሄ ለመሻት የትኛው አማራጭ ከላይ ከተዘረዘሩት የስነ ምግባር ንድፈ ሃሳቦች ውስጥ የትኛው/የትኞቹ አግባብነት አለው/አላቸው?
5) የተመረጠውን የስነ ምግባር ንድፈ ሃሳብ (ሃሳቦች) ለመጠቀም የምናነሳቸው አቢይ ጥያቄዎች የትኞቹ ናቸው?
6) ለሚቀርቡት ጥያቄዎች የሚሰጡ መልሶች ምንድን ናቸው?
7) ከቀረቡት መፍትሄ ሃሳቦች ውስጥ የትኛው/የትኞቹ በስነ ምግባር መመዘኛ ሲታዩ የተሻሉ ናቸው?

## *ማጠቃለያ፡- የተመረመረ ሕይወት*

ስነ ምግባር እውነትን ከውሸት አንጥሮ ለመለየት፤ ጎጂውን ከጠቃሚው ነገር በትጋት ለመመልከት የሚያስችለንና ተገቢና ሚዛናዊ የውሳኔ አሰጣጥ መመሪያና ጥናታዊ እውቀት ነው። ስነ ምግባር ለባህሪያችን እድገትና እንፃት ማለትም በግልና በሙያዊ ሕይወታችን ውስጥ በጎ ምግባርንና በጎ ተግባርን የምንከተልበት፤ እንደ ሰብእ የምንነታችንና የማንነታችን መሠረት መገንዘቢያ የጥናት ማህደር ነው።

---

[53] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 30.

[54] ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 12.

[55] ባንክስ፣ ገፅ 269.

የፍትህ ሥርአቱ ባለሙያዎችም፣ ዳኞች፣ ዓቃብያነ ህግ፣ ጠበቆች፣ ፖሊሶች፣ የማረሚያ ቤት አስተዳዳሪዎችና ሠራተኞች (ስታፍ) ከሙያ እውቀታቸውና ሥልጠናቸው ጋር ስነ ምግባር ማጥናት የሚገባቸው፣ ለሕዝብ የተሻለ ማህበራዊና አስተዳደራዊ አገልግሎት ለመስጠትና የሙያ ኃላፊነታቸውን በአግባቡና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለመወጣት እንዲችሉ ነው።

የስነ ምግባራችን ምርምር መመዘኛ ወይም መለኪያ ከሆኑት መካከል ስድስቱን የስነ ምግባር ክፍሎች ያካደኑት ንድፈ ሃሳቦች፡- 1) ማህበራዊ ውል (Social Contractualism)፣ 2) የተጠቃሚነት ምግባርና ገቢር (Utilitarian Ethics)፣ 3) ግዴታዊ ስነ ምግባር (Deontology)፣ 4) ምግባረ ሰናይ (Ethics of Virtue)፣ 5) አንስታይ ስነ ምግባር (feminist ethics) እና 6) ፍትሃዊ ህሊና(Sense of Justice) ናቸው። እነዚህም ንድፈ ሃሳቦች ከላይ በተዘረዘሩት በቢሆን ስነ ምግባር (Normative ethics) እና በልዕለ ስነ ምግባር (Metaethics) ውስጥ ይጠቃለላሉ። እነዚህን የስነ ምግባር ንድፈ ሃሳቦች መሠረት አድርጎ በእለት ኑሮም ውስጥ ሆነ በሙያ ኃላፊነት ላይ፤ የሚያጋጥሙ የስነ ምግባር አጣብቂኞችን (ethical dilemmas) ለመፍታት የሚያስችል የገቢራዊ ስነ ምግባር (applied ethics) ቀመር ደግሞ ለምግባራችን እድገትና እንፃት ያስፈልጉናል።